# ታጠቅ

ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር

የቲዎሪ መጽሔት

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር የተዘጋጀ

ሰኔ 1962

# ታጠቅ

ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር

የቲዎሪ መጽሔት

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር የተዘጋጀ

አዘጋጅ፦ ነገደ ጐበዜ

ዋጋው አንድ ብር

ሰኔ 1962

## ግልፅ ደብዳቤ ለአገሩ ገለልተኞች

ዛሬ በሃገራችን የለውጥ አውሎ ነፋስ ማንገዋበሉ አይኑን ከፍቶ ለማየት የሚሻ ሁሉ ግልፅ ነው።የሚገርመው ታድያ፤በያለበት የኢትዮጵያ ህዝብ የጭቆናን ሃይሎች ባለው ሃይል እየተቋቋመ ወጣቱ፤ሽማግሌው፤ወንዱና ሴቱ በሚሰቃይበት፤ቤቱና ንብረቱ በሚፈታበት ወቅት "እኔ ገለልተኛ ነኝ" ለማለት የሚቃጣው አወናባጅ መብዛቱ ነው።ሁሉ "ገለልተኛ" ነው።ጉዳዩ አይመለከተውም።ይህ ታድያ እውነት ነው ወይ? ዛሬ የኢትዮጵያ ህዝብ የነፃነት ትግል እየተፋፋመ በሚሄድበት ወቅት በጨቋኝና በተጨቋኝ መካከል ሆኖ አስታራቂ፤ከዳር ሆኖ ታዛቢ መሆን ይቻላል ወይ? በፍፁም አይቻልም።በተያዘው ትግል ማንም ኢትዮጵያዊ ገለልተኛ ሊሆን አይችልም።ከሁሉ ይበልጥ የማንቀበለው ደግሞ አንድ አንድ የተማሩ "ገለልተኞች" ነን ሊሉን ሲሞክሩ ነው።ስንት ጊዜ እንለፍልፍ? በታሪክ ሃይል ከተወረወርንበት ለዘራፊ አዳሪነት፤አውቀንና ፈቅደን በግልፅ ወደ ህዝቡ እስክንሸጋገር ድረስ እኛም ዘራፊዎች ነን።ገለልተኞች አይደለንም።

ዛሬ በኢትዮጵያችን በየአውራጃው፤በየመንደሩ፤በየቀበሌው የሚፈፀመው ግፍ፤የሚበዘበዘው የህዝብ ሀብት፤የሚፈሰው የህዝብ እንባ ከመቸውም ይበልጥ እያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ ይመለከተዋል።የአስተዳደሩ (የቢሮክራቱ) ደመወዝ፤"የተቀምጦ-በላው" ሃብታም መንሸራሸሪያና መንደላቀቂያ፤ . . . ወዘተ እያንዳንዱ ገበሬና ላብ አደር እየተወጠረ ከሆዱ ነፍጎ፤ከሚስቱ ነፍጎ፤ከልጁ ነፍጎ የሚያስረክበው የላብ ፍሬ ነው።በተጨቋኙ የኢትዮጵያ ህዝብ ላይ፤በየቀኑ ለሚወርደው መከራ ሁላችንም እየጨመረ የሚሄድ ሃላፊነት አለብን።"የተማሩ ወጣቶች" የዚህ ብዝበዛ ተጠቃሚዎች በመሆናችን ራሳችንን እንደታዛቢ ቆጥረው ሌሎችን ማግረር ብቻ ከዚህ ሀላፊነት አያስጥላቸውም።ሳንወደውና ሳንፈቅደው ከተወረወርንበት የጨቋኞቹ ወገን አውቀንና ፈቅደን እስክንወጣና ከህዝብ እስክንደባለቅ ድረስ፤በየመንደሩ ከሚጉሳቆለው፤ከሚጉላላውና ከሚዋረደው ሃገረ ሰብእ ጋር መጉሳቆላችን፤መጉላላታችንና መዋረዳችን እስካልተሰማን ድረስ እኛም ጨቋኞች ነን።ገለልተኞች አይደ



ለንም።

በጭቆና ላይ ጭቆና፤በብዝበዛ ላይ ብዝበዛ እየተጨመረበት የሚሄደው የኢትዮጵያ ህዝብ ትእግስቱ አልቆበታል።ከእንግዲህ የነፃነቱንና የክብሩን ዋስትና መሳሪያውን አፈፍ አድርጎ ጨብጦ ጨቋኞቹን መቋቋም ብቻ መሆኑ ገብቶታል።በሚመጣው የሪቮሉሽናዊ ትንንቅ ለታዛቢና ለገለልተኛ ምንም ቦታ የላቸውም።የነፃነት ትግል የኳስ ጨዋታ አይደለም።ዳኛና ተመልካች የለውም።በህብረተሰቡ ውስጥ ያለ እያንዳንዱ ግለሰብ ከዚህ ወይም ከዚያ አንዱን ወገን የግድ መርጦ በሙሉ ሀይሉና በሙሉ ልቡ መሳተፍ ይኖርበታል።

ታዛቢ ሊኖር አይችልም የምንለው የዚህን ትንንቅ መነሾ፤የአውሎ ነፋሱን ሀይለኝነትና የሚጠበቀውንም ውጤት በመመልከት ነው።የነፃነት ትግል ረጅም፤አታካችና መራር ትግል ነው።ስርአተ ማህበራችን ድብልቅልቁ ወጥቶና ትንንቁ ተፈፅሞ የህዝባችን የነፃነት ትግል ከታሰበው ግብ ሲደርስ ማንም ሰው እንደቀድሞው አይሆንም፤ብዙ መሰረታዊ ለውጦች ይኖራሉ።አውሎ ነፋሱ ባለፈበት ሁሉ በግለሰቡ፤በቤተሰቡና በህብረተሰቡ፤በጠቅላላው በሃገሪቱ፤የቀድሞው የግዢና የተገዢ መንፈስ በሙሉ ተጠራርጎ ተጥሎ፤የአዲስ ኢትዮጵያና የአዲስ ኢትዮጵያዊ ፅኑ መሰረት በያለበት ስር ሰዶ እናገኘዋለን።መራራው ትግል አልፎ ፀሀይቱ ስትወጣ የቀድሞዋ ፀሀይ አይደለችም።ያኔ ለሁሉም ቃብራለች።የቀድሞ ኢትዮጵያዊያን ገዢም ሆኑ ተገዢ በአንድነት ድምጥማጣቸው ጠፍቷል።ከእንግዲህ አዲስ ሰው፤አዲስ ኢትዮጵያዊ ነው።

በአንድ ወገን በትግሉ ጊዜ ለነፃነቱና ለክብሩ ህይወቱን ለመሰዋት ቆርጦ የተናነቀ፤ደጋግሞ ከሞት አፋፍ እየደረሰ የተመለሰ፤የነፃነቱንና የክብሩን ዋጋ በእናቱ፤በአባቱ፤በእህቱ፤በወንድሙ፤በሚስቱ፤በልጁና በወዳጁ መከራ የከፈለ፤በባርነት ሞቶ በነፃነት የተነሳ፤ሊከፍል በተሰናዳው በህይወቱ ዋጋ ባርነቱን አሽቀንጥሮ ጥሎ ነፃነትን የገዛ፤ጭቆናን የማይወድ፤በትግልና በፈተና ወደሰብአዊነት የተነሳ፤አዲስና ኩሩ ሰው እናገኛለን።በሌላው በኩል ደግሞ ያለው እንደዚሁ በዚሁ በትንንቅ ጊዜ ለጨቋኝነቱ ዋጋ የሱ በሆኑት ሁሉ የከፈለ፤ራሱም በመከራ የተፈተነና ከቀድሞው የገዥነትና የበላይነት ልክፍት፤ስሜትና ቅዠት የአገሬው አፈ

ሙገ፤ አላቅቆት፤የሰው ልጅን እኩልነት በግዱ አምኖ የተቀበለ፤እሱም ወደሰብአዊነት የተመለሰ አዲስ ሰው ይሆናል።

በጭሩ ረጅም ትግላችን ሲፈፀም ይህ አውሎ ንፋስ በአስተሳሰባቸው ያልለወጣቸው፤በጥቅማቸው ያልነካቸውና ጨቋኞች እንደነበሩ እንደቀድሞ የሚጨቁኑ፤ተጨቋኞች እንደነበሩ እንደቀድሞው የሚጨቆኑ ሊኖሩ አይችሉም።ከዚህ ቅጥሎ፤ከዚህ ትንንቅ፤ከዚህ እሳት፤ከዚህ ድብልቅልቅ ውስጥ ገብቶ ሳይፈተን የሚወጣ ፍጡር አይገኝም።ታድያ እዚህ ውስጥ ከመሀል ሆኖ አስታራቂነት፤ከዳር ሆኖ ገለልተኝነት ይቻል ይመስላችኋል? እኛ አይመስለንም! ስለዚህ ዛሬ "ባትመርጡ" ነገ መሀል መቆም ሲቸግር የግድ በታችሁን እንድታስታውቁ ትገደዳላችሁ።

እዚህ ላይ በተለይ ለውጥንም ሆነ ባሉበት መቆምን በመፍራት በበዝባዦቹና በህዝቡ መካከል "ሶስተኛ መንገድ" ያገኛችሁ እየመሰላችሁ "ጥገናን" የሙጥኝ ያላችሁትን ምሁሮች የያዛችሁት መንገድ ምንም አይነት ዘለቄታ እንድሌለው ልናስታውሳችሁ እንወዳለን።ዛሬ በኢትዮጵያ የሚያስፈልገው ለውጥ የእያንዳንዱን ገበሬና የእያንዳንዱን ሰራተኛ በጠቅላላ የህዝቡን ኑሮ በይበልጥ የተሙዋላ የሚያደርግ ለውጥ ነው።ስለዚህም ህዝብ ጠላቶቹን ደምስሶ እድሉን እጁ ማስገባት አለበት። እናንት ህልማችሁ የበዝባዦችን ጥቅም ሳትተናከሉ፤ከዚህም የሚወረወርላችሁ ጉርሻ ሳይቆነጠርለት የህዝቡ ደህንነት ሳይሆን የህዝብ "ፀጥታ" የሚጠበቅበትን ዘዴ ለማግኘት ነው።ምንም መሰረታዊ ለውጥ ሳይደረግ "የሁሉ ኢትዮጵያዊያን" ጥቅም የሚጠበቅበትን ዘዴ ለማግኘት ትወድቃላችሁ፤ትነሳላችሁ፤ትተቻላችሁ፤ትፈለስፋላችሁ።በህብታምና በድሀ፤በጨቋኝና በተጨቋኝ የተከፈለ ህብረተሰብ ውስጥ "የሁሉንም ጥቅም" በአንድ ላይ እንዴት መጠበቅ ይቻል ይመስላችኋል? በሀገራችን ድሀ፤አልቃሽ፤ተበዝባዥና ተዋራጅ መኖሩ ግፈኛ፤በዝባዥና አዋራጅ በመኖሩ መሆኑን "የተማራችሁት ገለልተኞች" እንዴት አጣችሁት? በአንድ ሀገር፤በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ ይቆራኙ እንጂ ድሃና ሃብታም እኮ የሚኖሩት ሁለት አለም ውስጥ ነው! የህዝብ ነፃነት አለ፤የበዝባዦች ነፃነት አለ፤የህዝብ እውነት አለ፤የበዝባዦች እውነት አለ።የህዝብ ፍትህ አለ፤የበዝባዦች ፍትህ አለ።የህዝብ ደህንነት አለ፤



የበዝባዦች ደህንነት አለ።የበዝባዦች መብት ህዝብን መጨቆን ነው።የህዝብ መብት ደግሞ የነሱን ጭቆና ተናንቆ መጣል ነው።ነፃነታቸው ከሁሉ አስቀድሞ እንደልብ የመዝረፍ ነፃነት ነው፤የህዝቡ ነፃነት ደግሞ ከሁሉ በፊት ዘረፋን መቋቋም ነው።የበዝባዦች ሀብት መሰረቱ የህዝቡን ላብ መግፈፍ ነው።የህዝብ ሀብት መሰረቱ ሁሉም የላቡን ፍሬ አለመግፈፉ ነው።ባጭሩ ለህዝቡና ለበዝባዦቹ አንድ ትርጉም የሚሰጠው ምንም ቃል የለም።ስለዚህም በበዝባዦች ስርአት ውስጥ በአንድነት "የሁሉም" ጥቅም የሚጠበቅበት ምንም አይነት ተአምር ሊኖር አይችልም።ዛሬ የነሱ ነፃነት የህዝብ ባርነት ነው፤ነገ የህዝብ ነፃነት የነሱ መደምሰስ ይሆናል።

ስለዚህ ሺህ አመት ብትመራመሩ፤ሺህ ኮሚስዮን ቢፈጠርላችሁ፤ሺህ ሚኒስቴር ቢቋቋም፤የበዝባዦቹ ጥቅም ከመሰረቱ ሳይነካ የኢትዮጵያን ህዝብ ጥቅም ማዳበር አይቻልም።

እንደዚህ "እጥንታችሁ" ከላይ ለህዝቡ የምትወረውሩለት በወረቀት ላይ የሚውል "የመሸሸል" ፕላን ህዝቡ የሚያስፈልገውን ጠቅላላ ለውጥ ሊያስገኝለት አይችልም።ዛሬ በሀገራችን የጥገና ለውጥን ጠልተን መሰረታዊ ለውጥን የምንሻው የነገው ኢትዮጵያዊ በአካሉ የፋፋ፤በአስተሳሰቡና በመንፈሱ የዳበረ፤በእውቀቱ የላቀ፤ከተውተበተበበት የሰው ልጅ መንፈሳዊ ኩራት ጠንቆች ፈፅሞ የተላቀቀ ሙሉ ሰው እንዲሆን ስለምንመኝ ነው።"መሬት ላራሹ" ስንል አላማችንና ትግላችን አራሹ በያለበት የላቡን ፍሬ ሳይቀማ ለራሱ ለቤተሰቡና ለህብረተሰቡ ደህንነትና እርምጃ ያውለው የሚል የእንጀራ ትግል ብቻ አይደለም፤"መሬት ላራሹ" ስንል ህዝባችን ከላቡ ፍሬ ጋር፤ከመሬቱ ጋር፤አብሮ የተቀማውን በራሱ ያለውን እምነት፤በሰርቶ አዳሪነቱ ያለውን ኩራቱ እንደገና ተጎናጽፎ የተገፈፈውን ሰብአዊነቱን መልሶ እንዲያገኝ ነው።"መሬት ላራሹ" ስንል ባላባቱ ደግሞ እንደዚሁ ከሚዘርፈው ሀብት ጋር የሚያገበስብሰውን የሰርቶ አዳሪነት ጥላቻና ንቀት ተላቆ እሱም ወደሰብአዊነት የተመለሰ ፍጡር እንዲሆን ነው።ስለዚህም የነፃነት ትግላችን ሙሉ ውጤቱን አስገኝቶ ህዝባችን ከማንኛውም ልክፍት ስሜቶችና የሰው ልጅ መንፈሳዊ ኩራት ጠንቆች የሚላቀቀው ከናንተ እንደሰማይ መና በሚወርድለት

የጥገናዊ ለውጥ ችሮታ ሳይሆን ራሱ በትግሉ ተደራጅቶ ይገባኛል ብሎ ሲወስድና ይህም ትግል ለሚያስከትለው መስዋእትነት ዝግጁና ብቁ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው።

ለኢትዮጵያ ህዝብ የሚያስፈልገው መሰረታዊ ለውጥ በዚህ ወይም በዚያ ፀሀፊ ጥረት የሚገኝ ነገር አይደለም።ይህ መሰረታዊ ለውጥ እያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ፣ህዝቡን በሙሉ፣የሚመለከት ጉዳይ በመሆኑ የኢትዮጵያ ህዝብ በሙሉ ተደራጅቶና ተጋግዞ በሚያደርገው ጥረት የሚገኝ ጠቅላላ ለውጥ ነው።እንደዚህ ያለው የህዝብ ጥረት ፍሬ እንዲሰጥ ከተፈለገ አስቀድመው የህዝብ ጠላቶች ከሀገራችን ገፅ መጥፋት አለባቸው።ይህ ጥረት ለጊዜው ከሁሉ ተቀዳሚነት የሚሰጠው የነፃነት ተጋድሎ ነው።የህዝቡን ወገን የመረጡ በምንም ፀረህዝብ ፕሮፓጋንዳ ሳይወናበዱና ሳይጭበረበሩ፣ይህን ትግል ይበልጥ ለማፋፋምና ለማደርጀት የማይቆጠብ ጥረት ያደርጋሉ።የህዝቡን ጠላቶች አውቀውም ሆነ ሳያውቁ የመረጡ ደግሞ ይህን የነፃነት ተጋድሎ በየምክንያቱ እያንቋሸሹ አጉል ተስፋ በመስንዘርና የማያዋጣ የጥገናዊ ለውጥ ጉዳና በማሳየት የህዝቡን ትግል ለመግታት፣ለማድከምና ለማጭበርበር ይጥራሉ።በነዚህ በሁለት ተቃራኒ መንገዶች መሃከል ሶስተኛ መንገድ ሊኖር አይችልም።

ይልቁንስ ተነሱ! ዛሬ እያንዳንዱ የተማረ ወጣት ታላቅ የትውልድ አደራ አለበት።ይህ የትውልድ አደራ ገለልተኛ ነኝ እያሉ እንደሰጐን አይን መጨፈን አይደለም።ከዘራፊዎች ተደባልቆ መዝረፍ አይደለም።ከተበዝባዦች ተደባልቆ ለመራራ ልቅሷቸው ሙሾ ማውረድ አይደለም።የትውልዳችን ዋና አደራ ህዝባችን በረጅም የነፃነት ትግል ታሪኩ ደጋግሞ ባፈራቸው ተጋዳዮች አርአያነት በመመራት የኢትዮጵያችንን የእውነተኛ ነፃነት ቀን ለማብሰር ከሚታገሉ ሀይሎች ጋር ተደባልቆ ለዚህ ለተቀደሰ ተግባር መሰለፍ ነው።

---